


Info

t.me/BookAlem

Invite Link

@BOOKALEM

# ዝጎራ



ዝጎ፣

ዝጎ፣

ዝጎ፣

ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ

2010 ዓ.ም.

@BOOKALEM

# ዝጎሁ

ዓለማየሁ ዋሴ ክሸቴ (ዶ/ር)

ግንቦት 2010 ዓ.ም

@BOOKALEM

© ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ 2008 ዓ.ም.
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::
ALL RIGHTS RESERVED

ሁለተኛ ዕትም መጋቢት 2009 ዓ.ም
ሦስተኛ ዕትም ነሐሴ 2009 ዓ.ም
አራተኛ ዕትም መጋቢት 2010 ዓ.ም
አምስተኛ ዕትም ግንቦት 2010 ዓ.ም

አድራሻ
ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ (ዶ/ር)
E-mail:- Emegua2015@gmail.com
ባሕር ዳር
ኢትዮጵያ

ዋና አከፋፋይ፡-
አማረ አበበ ሞላ
+251 0920 18 79 06
ባሕር ዳር
ኢትዮጵያ




@BOOKALEM

## ለአዚህ መጽሐፍ

መግቢያ አያስፈልገዎትም። ጽሑፉ የፈደልና የሰዋሰው ግድፈት ቢኖረው ታግሰው እንዲያነቡት በታላቅ ትሕትና ተጋብዘዋል። ይህ ትረካ ለፍልስፍና፣ ለምክር ወይም ለተግሣጽ ታስቦ አልተጻፈም። ይልቁንም እውነተኛ ገጠመኞችን መሠረት አድርጎ በልብ ወለድ መልክ የተዘጋጀ ጽሑፍ ስለሆነ በዚህ ወከባና ጥድፊያ በበዛበት ዓለም ውስጥ ቢሆንም ጊዜ ወስደው ተረጋግተው ቢያነቡት እንዴት ደስ ባለኝ!

ጸሐፊው

መልካም ንባብ !

## ለውር ትኩዛዝ

## የጨለማው ጓዳ ብርሃን ሲያገኝ



@BOOKALEM

# ምዕራፍ አንድ

ሚ/ር ራምዚ አንቶን አቡዳቢ ካረፍንበት ሆቴል ይዞኝ የምሥራቅ አቅጣጫን ተከትሎ አምስት ብሎኮችን ከነዳ በኋላ አንድ ዘመናዊ ባለ20 ፎቅ ሕንጻ ሥር መኪናውን አቁሞ በአሳንሰር 18ኛው ፎቅ ላይ ከሚገኝ ሬስቶራንት ወሰደኝ። የፋርስ ባሕረ ሰላጤ አካል የሆነው ውኃ ተንጣሎ ይታያል። "ግሩም የሆነ ምርጫ ነው፣ አመሰግናለሁ" አልኩት።

ምሳ ቀርቦልን እየበላን ሳለ እንዲህ አለኝ፡-

"አባቴ ስለ ኢትዮጵያ ብዙ ነገር ይነግረኝ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ በቂ ግንዛቤ የነበረው ይመስለኛል" አለ።

"መልካም ነገር እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ" አልኩት።

"አዎን! ኢትዮጵያውያን በእምነታቸው ጠንካራ፣ ጀግኖችና ሀገር ወዳዶች ናቸው። እርግጥ ሲበዛ ምሥጢራውያን ናቸው" ይለኝ ነበር አለ።





@BOOKALEM

# ምዕራፍ ሁለት

ከዱባይ ተመልሼ ባሕር ዳር ኤርፖርት እንደደረስኩ በፍጥንት ወደ ቤቴ ሄድኩ። ቤት ውስጥ በተገቢው መንገድ ሰላምታ እንኳን ሳላቀርብ ቀልፌ ካስቀመጥኩበት ኮመዲኖ ብራናውን አውጥቼ ዘረጋሁ። ያው ከላይኛው ጠርዝ መካከል ላይ ከተጻፈው ራእይ 22፥5 በስተቀር አሁንም ሌላ ነገር የለም።

አቡዳቢ እስከ ሄድኩበት ጊዜ ድረስ በተአምር ጽሑፍ ያመጣልኝ ይመስል ብራናውን ቧትም ማታም ሌሊትም ንቅቼ ሳየው እንደነበር አስታውሼ ፈገግ አልኩ። የሚገርመው ግን አቡዳቢ ሆኜ ካየሁት በመነሣት ወረቀቱ በስውር ተጽፎበት ይሆናል ከሚለው ፍንጭ በስተቀር በስውር ተጽፎ ቢሆን እንዴት ነው ፊደላቱን ካለመታየት ወደ መታየት ማምጣት የሚቻለው የሚለውን በደንብ አለማሰቤ ነው። እናም እንደ ‹አል አይን ብሔራዊ ሙዚዬም› በተለየ መብራት ከመጠቀም ውጭ በሌላ በምን ዘዴ እንደሚገለጽ አለመጠየቄን ሳስበው በታ በጣም ስሜታዊና ግልብ፣ በቀላሉ የምደሰት፣ በቀላሉ የማዝን መሆኔን ተገነዘብኩ።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ ሦስት

በተቀጣጠርንበት ቦታ ስንገናኝ ዶ/ር ክብረ በዓል ጥብቅ አድርጐ አቀፈኝና፡-

"ወንድም ሲሳይ! ከዚህ ሆኜ አንተ ወደ ውጭ ሀገር በሄድክ ቁጥር የሆን አካሌ ተቆርጦ የሄደ ይመስለኛል" አለኝ።

"እንዴ በዚያው ብቀር እንዴት ልትሆን ነው?" አልኩት ወንድማዊ ፍቅሩ እንጀቴን እያንሰፈሰፈው።

"እንጃ! ብቻ መጥቼ እንጠልጥዬ የማመጣህ ይመስለኛል" አለኝ እየሣቀ

"ይልቅ ደስ ብሎኛል" አልኩና እጁን ጠበቅ አድርጌ ጨብጬ አወዛወዝኩት።

"ምን ተገኘ?" አለኝ።



@BOOKALEM

“አይይ! በተለይ መድኀኒት ነክ የሆኑ ዕፀዋትን ከእኔ የበለጠ አንተ የሠራህበት አይደለም እንዴ?” አልኩት ባለመስማማት።

“ቢሆንም እነዚህን ስሞች ሰምቼ አላውቅም” አለና ማዶ ማዶ እያየ “በዚህ ምርምርህና ፍለጋህ ውስጥ ከሎጅስቲክ ድጋፍ ውጭ ለመሣተፍ አቅሙም ዕውቀቱም ያለኝ አይመስለኝም” አለ።

“ኢዲያ! አንተ ደግሞ! አሁንስ አባ መዝገበ ሥላሴን ሆንክብኝ” ብዬ ስመናጨክ ዶ/ር ክብረ በዓል ከጣራ በላይ ከት ብሎ ሣቀ። እንደዚህ ሲሥቅ አይቸው አላውቅም!

የሣቁ ምክንያት የገባኝ ግን ሰንባብቼ ነበር።





# የውዴታ ግዴታ

## መርቤ ፈካጊ ማሊሻ ቢያነቃቀው አያየውም



@BOOKALEM

# ምዕራፍ ኣሩት

አስፈሪውንና አስደናቂውን ትእዛዝ ከተቀበልኩ በኋላ እጅግ መረበሽና መጨነቅ ጀመርኩ። ያም ሆኖ አጉል ደፋሩና ምሥጢር የሚያቃትተው ልቤ ያመጣብኝ በመሆኑ እንደተነገረኝ ከመፈጸም ውጪ አማራጭ አልነበረኝም።

የታዘዝኩትን ዕፆች ዐይነትና የሚገኙበትን ስፍራዎች በብዙ ድካም በአስገራሚ ሁኔታ ከተጻፈው የብራና ማስታወሻ ላይ ከተረዳሁ በኋላ ለፍለጋው ከምሠራበት መሥሪያ ቤት የዐሥር ቀን ፈቃድ ወሰድኩ። ፍለጋውን ለመጀመር ሁሌም ለምርምር ሥራዩ መስክ ስወጣ መኪና የሚያከራዩኝ ወዳጄ ዘንድ ሄጄ 2H ላንድክሩዘር ተከራየሁ።

"እውላላ ሜዳ ላይ ቆሜ እንዳልቀር መኪናውን በደንብ ፈትሽልኝ። ቢበላሽ መጠገን ይቅርና ምን እንደተበላሸ እንኳን ማወቅ የምችል አይመስለኝም" አልኩት የመኪና አከራዩን።

# ምዕራፍ አምስት

ቀደም ብዬ ወደ መተማ ለመምጣት ከአባ ክንፈ ሚካኤል ጋር ከተነጋገርኩ በኋላ የገዳሙን የቆላ ቀርቀሃ ልማት በተመለከተ ከገዳሙ አባቶች ጋር ለመወያየት ከክልሉ የደን ባለሙያዎች እንደሚሄዱ መረጃው ስለበረኝ የጉዞ ቀኑን ከእነርሱ ጋር ባቀናጀሁት መሠረት ገንዳ ውኃ ከተማ ተገናኘን።

በማግስቱ ቀደም ብለን ለመሄድ በተስማማነው መሠረት ከገንዳ ውኃ ከተማ ተነሥተን ደረቅ ዐባይ ከተባለችው መንደር ስንደርስ ገና ከጠዋቱ 12፡20 ነበር። አባ ክንፈ ሚካኤል በነገሩኝ መሠረት ቄስ ገዳሙን አጠያይቀን አገኘናቸው።

ቄስ ገዳሙ ጠይም ቀጠን ብለው ረዘም ያሉ ከአለባበሳቸው አንጻር ሲታዩ ደግሞ ጨዋ ነጋዴ እንጂ ካህን አይመስሉም። በኋላ ላይ ትሕትናቸውንና ቅንነታቸውን ሳስተውል ግን ‹እውነትም ካህን› ብያለሁ። በንግድ ሥራ የሚተዳደሩ ሲሆን በአካባቢው የሚገኘው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪም ሆነው እያገለገሉ ሲሆን በተጨማሪ ለማኅበረ ሥላሴ ገዳም መነኮሳት እንደ ወደብ ወይም መናኸሪያ ሆነው ያገለግላሉ። የእኛ ቢጤ እንግዳ ሲመጣም ሥራቸውን እርግፍ



@BOOKALEM

ጥያቄያችንና ውይይታችን ማለቂን ሲረዱ የስጋጃ ምንጣፍ እስኪጠፉና እንድንገበረከክ ጠየቁን። ከሌሎች ሁለት መነኮሳት ጋር ሆነው ጸሎት ካደረጉ በኋላ በትልቅ የእንጨት መስቀል ጀርባችንን እየዳሰሱ ጸሎት አደረጉልን። የሆነ ነገር ከላዩ ላይ ለቆኝ የሄደ መሰለኝና፦

"እንደ ውኃ ባልዲ በራሴ ላይ አጋንንት ተሸክሜ ነበር እንዴ የምዞር! ወይ ጉድ!" ስል ዳዊት "ምን አልክ?" አለኝ። በልቤ የማንሾካሹከ መስሎኝ ለካስ ከአፌም ተሰምቶ ኖሯል።

"አይ! የጸበሉ ነገር ገርሞኝ ነው እንጂ" አልኩ እንደማፈር እያልኩ።



# ምዕራፍ ስድስት

ጸሎቱ ሲያበቃ ሰው ወደ ውጭ ሲወጣልኝ የመጣሁበትን እጠይቃለሁ እያልኩ ስዘጋጅ አባ ኪዳን ማርያም፦

"እስኪ አካባቢውን ላስጎብኛችሁ ተከተሉኝ" አሉና ከሰሜን አቅጣጫ ከሚገኘው ቤታቸው የምዕራብ አቅጣጫን ይዘን የቤተ ክርቲያኑን የግንብ አጥር በስተውጭ ተከትለን መራመድ ጀመርን። ከዱር እንጨት የተዘጋጀች ቀጭን ከዘራ ይዘዋል። ከፊት ለፊት ሲራመዱ መሬቱን የሚረግጡት አይመስልም። በቃ ረጋ ያሉ ሲናገሩ ፈገግታ የማይለያቸው ናቸው።

አባ ቀጠሉና "ሁሉም መናኝ የራሱ መኖሪያ በኣት አለው። በተጨማሪም መፀዳጃ ቤት እንዲኖረው የግድ ነው" አሉ።

አካባቢው ዛፎች ከፈጠሩት ቀዝቃዛ ድባብ በተጨማሪ ፅዳቱ ልዩ ግርማን አላብሶታል። ከወፍ ጫጫታ ውጭ የሚሰማ ቢኖር ‹እሽም እሽም› የሚለው በእጅ የሚገፋ የድንጋይ ወፍጮ ድምፅ ብቻ ነው።



@BOOKALEM

በማግስቱ የበረሓ ጓደኞቼን ተሰናብቼ ወደ ጎንደር አቀናሁ። ጎንደር አንድ ቀን ካረፍኩ በኋላ ሁለተኛውን ዕዕ ወደማገኝበት ገዳም መሄድ አለብኝ።

"ወደ ቅዱሱ ቦታ ለመመለስ በዘገየህ ቁጥር የኋለኛው ዘመንህ እንደምንጣፍ ወደ አንተ እየተጠቀለለ ይቀርባል!"

የተባልኩት ከአእምሮዬ የሚጠፋ አልሆነም። ዕድሜ ነውና መሽቶ በነጋ ቁጥር እያጠረ መሆኑን ማሰብ ያስጨንቃልና!





# ምዕራፍ ሰባት

ከጎንደር ከተማ በጠዋት ቀደም ብዬ ጉዞ ጀመርኩ። ረጅምና አድካሚ ጉዞ ይጠብቀኛል። እንደ ዕቅዴ ከሆነ የሊማሊሞን ቁልቁለትና የተከዜን በረሓ ከሰዓት በፊት አቋርጬ ከሰዓት በኋላ የሽሬ ሜዳዎችን ዐልፌ አመሻሹ ላይ አክሱም ገብቶ ለማደር ነው። የጉዞ መዳረሻዬ አክሱም አቅራቢያ የሚገኝ ጥንታዊ ገዳም ነው።

አምባ ጊዮርጊስ ከተማን ሳልፍ ፀሐይ ሙሉ ለሙሉ የወጣች ቢሆንም ሊማሊሞ አፋፍ ላይ ከምትገኘው ደባርቅ ቁርስ ለመብላት ፈለኩ። ስለዚህ የወገራ ሜዳን እያደነቅሁ መንዳቴን ቀጠልኩ። ይህ አካባቢ

"እኔስ እሄዳለሁ ከእያሌው ብሩ አገር

ጎፈሬው ተንዶ ተያዟል በማገር"

ተብሎ የተገጠመለት ነው። የሚገርመው የደጃች አያሌው ብሩ የትውልድ አካባቢ በጌምድር ጋይንት ቢሆንም የሰው ልጅ ሀገሩ ተግባሩና ምግባሩ እንደተባለው በጀግንነትና በቅንነት



@BOOKALEM

"ስማ አታ ፍትሕዊ መኪናዋን ወደ ውጭ አውጣለት" አለው በትግርኛ።

ወደ እርሱ ተጠግቼ እጆቼን ዘርግቼ አቅፌ ላመሰግነው ስራመድ እየና፡-

"ዋይ አታ ወዲ! ቆሻሻ ቱታ አይታይህም እንዴ!" አለ ወደ ኋላ እየሸሸ።

የሚገርመው ንግግሩ ሁሉ ቁጣ የተሞላ ይመስላል። ደግነትና ቁጣ ተደባልቆ ሲነገር የሆነ ልብ የሚሞላ ፍቅርና ቅንነትን ያሳያል። እናም ለራሴ፡- "የትግራይን ሕዝብ ፍቅር ኃላፊ ጊዜ በፈጠረው ውዥንብር ሳትዘናጋ እርሱን እንደ ጥሩ ጠላ ገፊት አፍ እያልክ ከሥር መጠጣት ይገባሃል" አልኩት።



# ምዕራፍ ዘጠኝ

ከአባ ወልደ አረጋዊ ጋር በተቀጣጠርነው መሠረት ከጠዋቱ 12:00 ሲሆን ከአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በር ላይ ሲጠብቁኝ አገኘኋቸው። ቢጫ የመነኩሴ ቀሚስና ከላይ እንደዚሁ ከሱፍ ክር የተሠራ ቢጫ ጋቢ መሳይ ነገር ለብሰዋል። አንዲት እነስ ያለች ቦርሣና መደገፊያ ከዘራ ከመያዛቸው ውጭ ባዶእቸውን ናቸው ማለት ይቀላል።

አባ ጸሎት ካደረጉ በኋላ ወደ አድዋ የሚሄደውን መንገድ ተከትለን የአክሱም ከተማን ለቀን ጉዟችንን ጀመርን። አክሱምን እየራቅን ወደ አደዋ በተጠጋን ቁጥር ታሪካዊዎቹን የአድዋ ተራራሮች በጀግንነት እንደተከፈሱ በሩቁ ማየት ጀመርኩ። ከመንገዱ ዳር አንድ ግማሽ አካሉ ዐፈር ደለል ውስጥ የተቀበረና የተቃጠለ የታንክ ቅሪት እየሁና አባን እንዲህ አልኳቸው፡-



@BOOKALEM

"አባታችን እባክዎት ትንሽ ፍራንክ ለአንዳንድ ወጪ ልስጠዎት" አልኳቸው ።

"አያስፈልገኝም። የምፈልገውንማ እኮ አደረክልኝ። ተባረክ የኔ ልጅ" አሉ ።

"ታዲያ የመጡበትን ሲጨርሱ ለምን በባሕር ዳር በኩል መጥተው ቤተሰቤን ቢባርኩልኝ ምን አለ?" አልኳቸው ።

"እስቲ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ" አሉ ።

"እንዴ! አለበለዚያ እኮ ደግሜ አላገኝዎትም ማለት ነው?" አልኳቸው ቅር እያለኝ ።

ፈርጠም ብለው "እንገናኛለን አንጂ የኔ ልጅ!" አሉና ጸሎት አድርገው አሳልመው ትክሻዬን ስመው ሸኙኝ።



# ጥንተ ነገር
## ካሳ ታርጋኚ ዘንዶ ያወጣል



@BOOKALEM

# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

ወደ ከተማው መሐል ሄጄ የለመድኩት ቦታ ኅብረት ሆቴል ምላ በላሁና የእንግዳ ማረፊያው አካባቢ ሆኜ ቡና ልጠጣ ስዘጋጅ ሺፈራው ቁጭ ብሎ አገኘሁት። ረጅም ጊዜ ተለያይተን የቆየን ይመስል ተቃቅፈን ሰላምታ ተሰጣጣንና፡-

"እንዴት ነው ነገሩ ወደ መተማ ሄድን ብላችሁ ደብረ ታቦር ተገኘህሳ?" አለኝ።

"አንተስ ጭልጋ አይከል ብለህ እንዴት እዚህ ተገኘህ" አልኩት በተራዬ ።

"እኔማ ከዚህም የግንባታ ፕሮጀክት ስላለኝ የጭልጋውን ችግር ከፈታሁ በኋላ በዚሁ መጥቼ ቃኝቼ ልሂድ ብዬ ነው" አለኝ።

"የጭልጋው ችግር በቀላሉ ተፈታልህ እንዴ?" አልኩት።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

ኹሉም የጥናት ቡድኑ አባላት በተሰጠው ማሳሰቢያ መሠረት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ደብረ ታቦር ከተማ ካረፍንበት ጎብረት ሆቴል፥ መሰብሰቢያ ክፍል ተገኝተዋል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ለዘመናት ተጠብቀው በቆዩት ቅርስ የተፈጥሮ ደኖች ላይ ለምናደርገው ሥነ ምህዳራዊ ጥናት ከተለያዩ ሀገሮችና ዩኒቨርሲቲዎች የጋበዝናቸው ልምድ ያላቸው ተመራማሪዎች ተገኝተዋል።

የምርምር ፕሮጀክቱን የምናስተባብረው እኔና አሜሪካዊቷ ዶ/ር ጄኔት ነን። የሎጅስቲክና ከሚመለከታቸው አካላት ሕጋዊ ፈቃድ ማግኘታችንን በማረጋገጣችን የመስክ ሥራችንን ለመጀመር የተግባር መርሐ-ግብርና የሥራ ድልድል ለማድረግ ነበር ውይይቱ የተዘጋጀው።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

ከአሜሪካውያን የምርምር ተባባሪዎቼ ጋር ከተለያየን ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ ከፈረንሳይ ከመጣሁ ከሁለት ሳምንት በኋላ ለፐ/ር ሃሮልድና ለራሴም ቃል በገባሁት መሠረት ወደ ሞገደኛው ደን ሳይት 09 ለመሄድ በጠዋት ተነሣሁ።

ወደዚህ ጥንታዊ የቤተክርስቲያን ደን ለመሄድ ከባሕር ዳር በሁለት አቅጣጫ መሄድ ይቻላል። ይሁንና ረዘም ቢልም ለስላሳው መንገድ በደብረ ታቦር በኩል በመዞር በመሆኑ በዚሁ በኩል ለመሄድ ወሰንኩ።

የመጀመሪያው ሥራዬ አድርጌ የወሰድኩት ዶ/ር ክርስቶፈር የሰጠውን መላምት ለማረጋገጥ የዐፈርና የድንጋይ ናሙና ወስጄ የብረትና የዩራኒየም ክምችት መኖሩን መፈተሽ ነው። ዐፈሩ የተለመደው ዐይነት ቢሆን ከዚያ ዐልፎ ምን ምርመራ ማድረግ እንዳለብኝ አጠቃላይ ምሥጢሩንም እንዴት መፍታት እንደምችል ምንም ሐሳብ የለኝም። ብቻ ግን እስከመጨረሻው ተጉዤ ምሥጢሩን ለመረዳት እንደወሰንኩ ግን ልቡናዬ ተገንዝቧል።





@BOOKALEM

# ምዕራፍ ዐሥራ አራት

ከሞገደኛው የቤተ ክርስቲያን ደን ተመልሼ ባሕር ዳር በጊዜ ገባሁ። መንገድ ላይ እያለሁ ወደ አዲስ አበባ የአውሮፕላን ትኬት ለማግኘት በጸሐፊዩ በኩል አስመዘገብኩ።

ማታ ባለቤቴን፡-

"ነገ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ አስቢያለሁ" አልኳት።

"አንተ በቃ እንደ ዘላን ብድግ እያልክ መሄድ ሥራህ ሆነ ማለት ነው? ዛሬ ደግሞ ምን ተገኘ?" አለችኝ ።

"በጣም ወሳኝ የሆነ የዐፈር ናሙና ለማስመርመር ነው" አልኳት ።

"ሊሆን ይችላል። ግን ዛሬ ከመስክ ነው የመጣህ። ለምን እያረፍክ አትሠራም?" አለች ለዘብ ብላ ።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

ከፕሮፌሰር ሃሮልድ ጋር በSkype በተገናኘን በ13ኛው ቀን መማሪያውን እንደላኩትና ከሁለት ቀናት በኋላ ባሕር ዳር መረከብ እንደምችል ነገሩኝ። ደስታዬ መጠን አልነበረውም። እንዳሉትም በሁለተኛው ቀን ፕሮፌሰር ፓዎል የሚባሉ አሜሪካዊ ካረፉበት ሆቴል ሄጄ እንድቀበላቸው ስልክ ደወሉልኝ። ከዐሥር ቀናት በኋላ እንደሚመለሱና መማሪያውን መልሶ መውሰድ እንዳለባቸው ስለነገሩኝ እንድ ቀን ቀደም ብዬ እንዳመጣላቸው ተስማምተን መማሪያውን ተቀብዬ እርሳቸውንም አመስግኜ ወደ ቢሮዬ በረርኩ።

የሰዓት ልዩነቱን ጠብቄ ወደ ፕሮፌሰር ሃሮልድ በ Skype ደወልኩ። ከሠላሣ ደቂቃ በኋላ ድ.ጋሜ እንድንገናኝ አሳስበውኝ የመማሪያውን ባለቤት ጓደኛቸውን ፕሮፌሰር ኮሊንን እንደሚያገናኙኝ ተነጋገርን።

ኮሊን የፊዚክስ ፕሮፌሰር ሲሆኑ በተለይ በሥነ-ዕይታ (Optics) ላይ እንጋፋ ተመራማሪ እንደሆኑ ከፕ/ር ሃሮልድ ተረድቻለሁ። በኮምፒውተር ስክሪን ላይ ሲታዩ የሃምሳ ዓመት አካባቢ የሚሆኑ ሙሉ ጺማም ናቸው። የራሳቸው ጸጉር የዐይናቸው ቅንድብ ድረስ



@BOOKALEM

"አይ ልጄ፣ እኔ ይህ ሁሉ ምን ያደርግልኛል? የሚቸግረኝ ነገር የለ። የቸገረኝንማ መነጥሩን ነግሬሃለሁ" አሉ።

"አባታችን ስጦታ ነው። ስጦታን ደግሞ መርቆ መቀበል እንጂ ምን ያደርግልኛል ይባላል?" አልኳቸው በትሕትና።

"አይ ልጄ እንዲያው ያለችግራችሁ ተቸገራችሁ ብዬ ነው እንጂ" አሉና "ተባረኩ ልጆቼ" ብለው የእኔንም የባለቤቴንም የክርስትና ስም ጠይቀውኝ ነግሬያቸው ጸሎት አደረጉና እንደገና መስቀል አሳለሙኝ። ያመጣሁላቸውንም ዕቃ ወደ ፎቱ ወስደው አስቀምጠው ተመለሱና ወደ ሥራቸው አቀረቀሩ ።"





# ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

"አባ መዝገበ ሥላሴ ሰው ሲያነጋግሩ ወይም ሲጸልዩ ካልሆነ በስተቀር በሌላ ጊዜ በፍጥነት በሥራቸው ይጠመዳሉ። ታዲያ ለየት የሚያደርጋቸው በሥራ ላይ እያሉ ያለማቋረጥ ያዜማሉ። ብዙ ጊዜ የሚያዜሙት የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ድርሰት የሆነው ሰዓታት የሚባለውን ነው። ሌላ ጊዜ ውዳሴ ማርያምና ሌሎች የማላውቃቸውን የማሕሌት ዜማዎችን ያዜማሉ። ድምጻቸው ቀጠን ያለና የሆነ ጉልበት ያለው ማራኪ ነው።

በደን ግርማ በተከበበው ቤተ ክርስቲያን ከወፎች ዝማሬና ዐልፎ ዐልፎ እንደ ማጀቢያ ከሚደመጠው የጦጣዎች ድምፅ ጋር የአባ ዜማ ልብን ያሸፍታል። በተመስጦ ዝም ብዬ ሳዳምጥ ቆይቼ ድንገት እንደመባነን አልኩና፡-

"አባታችን የመጣሁበትን እረሳሁት እኮ! በስተምዕራብ ልሂድና ናሙና ይገኙ ልምጣ እንጂ" አልኳቸው።

"በል እኮ ሥራ አይደል፣ ሂድ" አሉና ተመልሰው አቀርቅረው ሥራቸውንና ማዜማቸውን ቀጠሉ።



@BOOKALEM

# የመጀመሪያው መጨረሻ



# ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት

መኪናዬን ሁሌ ከማቆምበት እርሶአደር ቤት ግቢ አቁሜ ወደ ቤተ ክርስቲያን አመራሁ። እንደተለመደው ዳገቱን ጨርሼ ከቤተ ክርስቲያኑ ደረስኩ። በስተስሜን በኩል ባለው በር ሄጄ ተሳለምኩና በጉጉት ወደ አባ መዝገበ ሥላሴ አመራሁ። ሁልጊዜም ሥራ ከዜማ ጋር ወይም መጽሐፍትን በማንበብ ተጠምደው በአታቸውን የማይለቁት አባ ግን በቦታው አልነበሩም። ለሠርክ ጸሎት ሄደው ይሆናል ብዬ ሰዓቴን ሳይ ገና ፀሥር ሰዓት ተኩል አካባቢ ነው። ግራ ተጋባሁ። ልጠይቀው የምችለው ሰውም በአካባቢው አልነበረም። ከቤተ ክርስቲያኑ ደረጃ ሄድኩና ፊቴን ወደ ዕቃ ቤቱ ወደ አባ የሥራ ቦታ አዙሬ የመኝታ ቀረጢቴን ተደግፌ ጋደም አልኩ።

ከፍተኛ ድካምና የቁስል ጥዝጣዜ ስለሚሰማኝ ዐይኔን ከድን አድርጌ ለማረፍ ሞከርኩ። ከአንድ ሰዓት በኋላ የሰው ኮቴ የሰማሁ መሰለኝና አይኔን ገልጬ ሳይ አባ መዝገበ ሥላሴ ከቤተልሔሙ አቅጣጫ ወደ እኔ ሲመጡ አየኋቸው። ከወትሮው በተለየ ነጭ ቀሚስ ከነጭ አስኬማ ጋር ለብሰው በላዩ ላይ ነጭ ጋቢ ቀኝ እጃቸውን አውጥተው አጣፍተው ለብሰዋል።

"የቅዱሳኑን ምሥጢር የምትከድን፣ ዐፈርና ውኃውን የምትጠብቅ፣ የእንስሳት የአዕዋፋቱ መጠለያ፣ የገዳማት የአድባራቱ ሞገስ፣ ቅዱስ ፍጥረት ሆይ! አንተን ሊቆርጥ ምሳር የሚስል እንዴት የተረገመ ነው?!" አልኩና ተነሥቼ እንደ ሰው እቅፍ አደረኩት።

የሆነ ሰላም እንደ ውኃ ሙላት ከራስ ጸጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ ሲያላብሰኝ ታወቀኝ። እንዲህ ያለ ሰላም በገንዘብም፣ በዕውቀትም፣ በሹመትም፣ በውርስም፣ በገጸ በረከትም የሚገኝ አይመስለኝም። ቢሆን ኖሮ ቀደም ብዬ አውቀው ነበር።

ወፎች ይዘምራሉ፣ ጦጣዎች ያሽካካሉ፣ የዛፎች ቅርንጫፍ በነፋስ ሽውታ እንደ ጸናጽል ይንሿሿሉ። እንደ ከዚህ ቀደሙ ድምፁ የሚያስበረግገኝ ሳይሆን በሆነ ጣዕምና ኅብረ ዝማሬ ለሰላሜ ማጀቢያ የሚያሸበሽቡልኝ መሰለኝ።

ስለብዙ ነገር ፈጣሪን ማመስገን የሚገባኝ ቢሆንም በዚች ምሥጢራዊትና ቅድስት ሀገር እንድኖር የፈቀደልኝን መሆኑን ሳስብ፡-

"ካደረገልኝ ነገር ውጭ ሌላ ሊያደርግልኝ የሚገባው ያላደረገልኝ ምን አለ?" አልኩ!

እጇን ከዛፉ አላቅቄ ዘወር ብዬ ልራመድ ስል የተጠቀለለ ብራና አየሁ። ለእኔ መሆኑ ገባኝና ገልጬ ሳየው በግልፅ ፊደላት፡-

"ኢትክስት ወኢትንግር ስመ ዝ ኀራ
እስመ አኮ መካነ ሁከት ወነገርጓር
ዘእንበለ መካነ ጸሎት ወአርምሞ"

"ይህ ተራራ የጸሎትና የአርምሞ እንጂ የግርግርና የወሬት አይደለምና ስሙን አትግለጸው" እንደማለት ነው።

"ከእንግዲህ ትእዛዛችሁን የምጥስ እኔ ማነኝ? እንደ ቃላችሁ ይሁን!"

ተፈፀመ//



@BOOKALEM




Info

t.me/BookAlem

Invite Link

@BOOKALEM